የ መኢሶን
ልሳን

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር—
መብትና ጥቅም
የሚታገል ጋዜጣ

ቁጥር 50 ቀን 30/5/69

## ዋናው ወሳኙ ነገር፣ የሕዝቦች አብዮታዊ ንቃትና ድርጅት

I

ከሌሎች አገሮች የአብዮታዊና የወዛደር ፓርቲዎች አነሳስና አስተዳደግ ታሪክ ጋር ሲመሳሰል፣ የመኢሶን ታሪክ በጣም የአጭር ጊዜ ታሪክ ነው።።መኢሶን የረጅም ጊዜ ታሪክና ልምድ ያለው ድርጅት አይደለም።።ገና ጀማሪ በመሆኑም፣ የኢትዮጵያን የወዛደር ፓርቲና ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባርን ለመፍጠር፣ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን ከግቡ ለማድረስና የሶሻሊስት ህብረተሰብን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ የማህበራዊ ኑሮና የባህል መሠረቶችን ለመጣል በሚደረገው የረጅም ጊዜ ትግል ውስጥ፣ አባሎቹ ሁሉ ገና ብዙ ይማራሉ።።

ይሁንናም፣ ማርክሲዝም–ሌኒኒዝም ስለአንድ አብዮታዊ ድርጅት የሚያስተምረንን አንዳንድ እውነቶችን፣ በዚህ በአጭር ጊዜ ታሪክ ውስጥ ድርጅታችን በገቢር ለማረጋገጥ ችሏል።። ከነዚህም ትምህርቶች ውስጥ አንዱ፣ በማንኛውም ጊዜ በአንድ ድርጅት ውስጥ ሁለት መስመሮች እንደሚኖሩ፣ በሁለቱ መካከል ትግል እንዳለና፣ እንደድርጅቱ ርእዮተአለማዊና ፖለቲካዊ ብስለት፣ ባንድ በተወሰነ ወቅት፣ ትክክለኛ ወይንም ስህተተኛ መስመር፣ ከሁለት አንዱ ሊያሸንፍ እንደሚችል ነው።።ትክክለኛ መስመር ወደፊት ያራምዳል፣ ውጤቶችን ያስገኛል፣ ስህተተኛ መስመር ወደ ሁዋላ ይጎትታል፣ ውድቀቶችን ያስከትላል፣ ካልታረመም ድርጅቱን ያቆረቁዝና በመጨረሻም ያጠፋዋል።።

ለአንድ ማርክሲስት–ሌኒኒስት ድርጅት የፖለቲካ መስመር ትክክለኛነት ዋስትና ሊሆኑ ከሚችሉት መሀከል ሁለት ነገሮች መጥቀስ ይቻላል።።እነዚህም፦ የወዛደሩን ርእዮተአለም በጥብቅ ለመከተል መቻል፣ ከሰፊው ህዝብ ጋር መተሳሰርና በሂስና በግለሂስ በሰፊው መጠቀም ናቸው።።

የወዛደሩን ርእዮተአለም በጥብቅ መከተል ማለት መፅሀፍትን ወይንም ጥቅሶችን በቃል ሸምድዶ እነዚያን በሆነ ባልሆነው ሁኔታ ሁሉ መልሶ ማስተጋባት አይደለም።።ወይንም ደግሞ በቃልም ሆነ በጽሁፍ አንዱን የህብረተሰብ ጥናት ሲገልፁ መፈክሮችን አከታትሎ ማስቀመጥ አይደለም።።እንደዚሁም በሌሎች አብዮቶች ሂደት ውስጥ የደረሱትን ሁኔታዎች ወይንም የተከናወኑትን ድርጊቶች ለመገልበጥ መጣጣር አይደለም።። የወዛደሩን ርእዮተአለም በጥብቅ መከተል ማለት ማርክሲዝም–ሌኒኒዝምንና የአብዮቶችን ታሪክ አጥንቶ፣ አዋህዶ፣ እነርሱን መሳሪያ፣ መፍቻ ቁልፍ በማድረግ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ መደቦችና አሰላለፋቸውን አበጥሮ ማወቅና በዚህ እውቀት ላይ በመመስረት፣ ተጨባጩን ሁኔታ የሚያንፀባርቅ የድርጊት መመሪያን ማውጣት ማለት ነው።። የዚህ አይነቱ አካሄድ ከአሳቦይነት፣ ከጥራዝ ነጠቅነትና ከገነዘነት ለመከላከል ይረዳል።።

ከሰፊው ህዝብ ጋር በጥብቅ መተሳሰር ማለትም እዚህ በጋዜጣ ቁጥር ከገበሬው ወይንም ከወዛደሩ ስብሰባዎች ፊት ቀርቦ ከተጨባጭ ኑሮው የራቁ፣ ግን በአብዮታዊ ቃላት የተሞሉ፣ ስለመደቦች፣ ስለቀራኔ፣ ስለፋሽሊዝም፣ ወዘተ.... የሚያስረዱ ከባድ ዲስኩሮችን ማድረግና ከዚያም ወደሌላ የግል ስራና ኑሮ እየተደሰቱ መመለስ አይደለም።።ከሰፊው ህዝብ ጋር መተሳሰር ማለት በመሃሉ መኖር፣ ስሜቶቹን፣ ፍላጎቶቹን፣ ችግሮቹን በሚገባ ማጥናትና በነዚያ ላይ ተመርኩዞ መፍትሄዎችን ለራሱ ለሰፊው ህዝብ አሳውቆ በመጠቀም ለነዚህ እንዲታገል አበርቶ መሰለፍ ማለት ነው።። የዚህ አይነቱ መዋሃድ በርግጥ ሁኔታን በደንብ ባይለዩ ትላልቅ ''መፍትሄዎችን''፣ እቅዶችንና አሳቦችን በከንቱ ከማቅረብ ያድናል።።

የወዛደሩን ርእዮተአለም በጥብቅ ስለተከተሉና ደግሞም ከሰፊው ህዝብ ጋር ስለተዋሃድን ዘለአለም ትክክለኞች እንሆናለን ማለት አይደለም።።ማርክሲዝም–ሌኒኒዝም የድርጊት መምሪያ ባይገባ ነው።። ነገር ግን ይህንን በሚገባ ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር የማገናዘቡ ነገር ቀላል ስላይደለ፣ በግለሰብ ደረጃም ሆነ በድርጅትስ ስህተቶች ይፈፀማሉ።።ሌኒን እንዳለው ደራሲ

በመጥቀስ ''ወዳጄ፣ ቴዎሪ ደረቅ ነው፣ የህይወት ዛፍ ግን ለምለም ነው'' ሲል፣ ህይወት፣ ህብረተሰብ፣ የተወሳሰቡ ነገሮች መሆናቸውን ነው የሚገልፀው::በዚሁን ጊዜ በግለሰብንነት /ሰብጀክቲቪዝም/ ውስጥ የሚወድቀው ነገሮችን እንደጥቁር ወይም ነጭ፣ በጣም ቀላል አድርጎ በመውሰድና ግንኙነቶቻቸውን ሁሉ በመርሳት ምክንያት ነው::ስለሆነም፣ ስህተቶች ይፈፀማሉ:: እነዚያን በጊዜውና በትክክል ለማረም ካልተቻለና ለዚህም ደግሞ ሂስና ግለሂስ በስራ ላይ ካልዋሉ፣ ከተፈሩና ከተተዉ፣ ያንዱን ድርጅት የፖለቲካ መስመር መዛባትና ውድቀት ያስከትላሉ::

መኢሶን በአጭር ጊዜ ታሪኩ ውስጥ እነዚህን የማርክሲዝም—ሌኒኒዝምን እውነቶች በገቢር ለራሱ ለማረጋገጥ ችሏል::ለዚህም ማስረጃ አንዳንድ ምሳሌዎች በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ይቀርባሉ::የዚህ ጽሁፍ አላማ በመኢሶን ውስጥ በየጊዜው የተነሱትን የመስመር ልዩነቶች ማሳየት፣ ድርጅታችን እስከዛሬ በኢትዮጵያ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የተጫወተውን ሚና በጥሩ መገምገም ነው::ግን እንግዲህ የዚህ አይነቱ ትንተና አሁን ባለንበት ወቅት ለምን አስፈለገ?ለዚህ ልዩ ልዩ ምክንያቶች አሉ:—

አንደኛ፣ ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ ድርጅታችን ከፍተኛ ተጋድሎን አድርጎ በተለይ ባሁኑ ወቅት ለትግሉ በጣም አመቺ ከሆነ ሁኔታ ላይ ደርሷል::የየካቲት እንቅስቃሴ ከጀመረበት አንስቶ እስከየካቲት 67 ገደማ፣ ለአንድ አመት ያህል፣ በደገፈው የንኡስ ከበርቴ ቡድንና በመኢሶን መስመሮች መካከል ምንም ያህል ልዩነት ሳይኖር፣ ድርጅታችን በየካቲት 67 የተለየ አቋሙን በያዘበት ወቅት ከደካማ ሁኔታ መነሳት ነበረበት::በ1967፣ በወዛደሩ እንቅስቃሴ፣ በመምህራንና በዘማቾች እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ ድርጅታችን የነበረው ጉልበትና ተደማጭነት የተወሰነ ሆኖ፣ ሜዳው በሙሉ ጉደሉ የንኡስ ከበርቴው ደንፋ ቡድን መፈንጫ እንደነበር ይታወሳል::ከዚያ ደካማ ሁኔታ ለመነሳት ያደረገው ያልተቆጠበ ጥረት ብዙ ቁራጥ ታጋዮችን አፍርቷል::እነዚህ ከአድሃሪው ''የግራ'' ክንፍ ድርጅትም ጭምር ተላቀው ከኛ ጋር የተሰለፉት ጓዶች የመኢሶንን የትግል ታሪክ ቢያውቁት የበለጠ ትምህርትና ጥንካሬን እንደሚሰጣቸው እናምናለን::ለወደፊቱም ቢሆን በድርጅታችን ውስጥ፣ ነገም ደግሞ በወዛደሩ ፓርቲ ውስጥ፣ የመስመር ትግሎች ይኖራሉ::ጓዶቻችን ሁሉ የማርክሲዝም—ሌኒኒዝም እውቀታቸውን ካዳበሩና በዚህ ርእዮተአለም ከተመሩ፣ ከሰፊው ህዝብ ጋር ከተቆራኙና በሂስና በግለሂስ ያለ ፍርሃት ከተጠቀሙ፣ ድርጅታችን ጠንክሮ፣ የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር በሚደረገው ትግል ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል::የድርጅቱን ታሪክ ማወቅ ለዚህም ይጠቅማል::

ሁለተኛ፣ በተለይ በ1968 በተደረገው ትግል ውስጥ፣ ''ሁለት መስመሮች'' የሚለው አባባል በአገራችን በጣም ተስፋፍቶ ነበር፣ አሁንም አለ::ወደድንም ጠላንም፣ ለብዙ ሰው ''ሁለት መስመሮች'' የተባሉት ከመኢሶንና ከኢሕአፓ ጋር ተዛምደዋል::ይሁንናም፣ ሌሎቹም የኢትዮጵያ ማርክሲስት—ሌኒኒስት ድርጅቶች ሃይለኛ ፀረደንፋ ትግል ማድረጋቸው የታወቀ ነው::ከነዚህ ድርጅቶች ጋር በመጀመሪያ ደረጃ ህብረትን፣ ከዚያም ውህደትን በመፍጠር የወዛደሩን ፓርቲ በጋራ ለመመስረትና ለመገንባት ጽኑ ፍላጎት አለን::እነዚህ የህብረት ጓደኞችን የመኢሶንን አጭር ታሪክ ቢያውቁ የበለጠ መግባባትንና መቀራረብን እንደሚፈጥር እናምናለን::የዚህ አይነቱ እውቀት አጉል ጥርጣሬንና አለመተማመንን ሊያስወግድ ይችላል::/በነገራችን ላይ፣ ''ሁለት መስመር'' የሚለው አሁንም ሆነ ወደፊት ሳይንሳዊ እውነትን ያዘለ ነው::የድርጅቶች በርከት ብለው መታየት ይህንን ሃቅ ፈጽሞ አይሰርዘውም::ባንድ በተወሰነ ወቅት፣ በአንድ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ሊታዩ የሚችሉት የተበጣጠሩ ሃይሎች ዞር ዞር ከሁለት አንደኛውን መስመር ያራምዳሉ::እንደሚባለው ሁሉ፣ በዚህ አይነቱ ወቅት ሁለት ሰፈሮች፣ ሁለት ፊናዎች፣ ሁለት አዝማሚያዎች፣ ሁለት ወገኖች ብቻ ናቸው ሊኖሩ የሚችሉት:: የተሰባጠረው አሰላለፍ የላይ ሽፋን ነው፣ ጊዜያዊ ነው፣ ስለሆነም ሊያሳስት ይችላል::/

ሶስተኛ፣ በልዩ ልዩ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ በተለያዩ ጊዜያት መኢሶን አቋሞችን ወስዷል::በተለይም በየካቲት 67 የድርጅቱ ጠቅላላ መስመር ከተለወጠና፣ መኢሶን ''አብዮታዊ ሂስ'' የሚለውን መመሪያ ወስዷል፣ በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ላይ ሊኖረው የሚገባውን አቀራረብ ከቀየሰ በኋላ፣ በልዩ ልዩ ነጥቦች ላይ [illegible] አቋሞች ይታወቃሉ::አንዳንዱ ሰዎች እነዚህን አቋሞች ድንገት ከሰማይ ዱብ እንዳሉ አድርገው ይመለከቷቸዋል::በነርሱ ላይ በድርጅቱ ውስጥ ተለቅ ትግል እንደተደረገ ስላላያውቁ፣ ወይንም ደግሞ ጠቅላላ የድርጅታችንን አቋሞችና ድርጊቶች በማገናዘብ ስላልተከተሉ፣ በተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ የተወሰዱት አቋሞች ባበሰሙት የተወሰዱ ሳይመስሉአቸው አልቀረም::ባሁኑ ሰአት የዚህ አይነቱ ጽሁፍ መውጣት እነዚህ ሰዎች ድርጅታችንን ይበልጥ እንዲረዱት ያደርጋል የሚል እምነት አለን::

አራተኛ፣ መኢሶን በኢትዮጵያ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ከታየበት ጊዜ አንስቶ በልዩ ልዩ ጥያቄዎች ላይ አቋሞችን ወስዷል::ከነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ በተወሰዱበት ወቅት ትክክል ሆነው፣ ዛሬ ግን ወደኋላ ተመልሶ ለተመለከታቸው ስህተተኛ ሊመስሉ ይችላሉ::ወይንም እርስበርሳቸው የሚቃረኑ ይመስላሉ::እነዚህ የተወሰዱበትን ሁኔታና አካባቢ ለማስታወስ ካልተቻለ፣ ተመልካቹ እራሱ ይሳሳታል::እንደዚህም የተወሰዱትን ትክክለኛ አቋሞች በሁኔታቸውና ባካባቢያቸው ውስጥ መልሶ አስቀምጦ ማየት እንደሚያስፈልግ ግልጽ ነው::

..../3

## II

ድርጅታችን መጀመሪያ ሲቋቋም በትግል ውስጥ ነበር የተፈጠረው፡፡እንደሚታወቀው ሁሉ፣ መኢሶን ከኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የፈለቀ ድርጅት ነው፡፡በፕሮግራሙ ውስጥ እንደተጠቀሰው፣ ወቅቱ የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል፣ የወዛደሩ፣ የአርሶአደሩ፣ የብሄረሰቦችና የተማሪዎች ትግል የተፋፋመበትና በአንፃሩም የሃይለሥላሴ ፊውዳላዊ መንግስት ህልውናውን ያባባሰበት ወቅት ነበር፡፡ስለሆነም፣ የአንድ አብዮታዊ ድርጅት አስፈላጊነት ግልጽ ነበር፡፡

በዚህ አይነቱ ሁኔታ፣ ድርጅቱን የመፍጠሩ ጥያቄ ሲነሳ፣ አብረውን ተሰልፈው ከነበሩት አብዮታዊ ምሁራንና ተማሪዎች ውስጥ በድርጅት አፈጣጠር ጥያቄ ላይ የቀኝና ``የግራ`` አስተሳሰቦች የነበሯቸው ይገኙ ነበር፡፡የቀኝ አድርባይነትን ያራምዱ የነበሩት፣ መፍጠር የሚያስፈልገው ``ሰፊ መሰረት`` ያለውና በጥብቅ ዲሲፕሊን ያልተሳሰረ የዲሞክራቶች ድርጅትን እንጂ፣ ማርክሲስት–ሌኒኒስት የሆነና በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት የሚመራን ድርጅት አይደለም ይሉ ነበር፡፡እነርሱ የፈለጉት መዋቅር እያንዳንዱ የድርጅት አባል ``ነፃ``/ሉዓላዊ/ ሆኖ የሚንቀሳቀስበትን መዋቅር ነበር፡፡ለዚህም ``የሉዓላዊ`` ጥያቄ የሰጡት ምክንያት፣ ሁላችንም ገና ለማርክሲዝም–ሌኒኒዝም አዲሶች ስለሆንንና አንዱ ሌላውን ሊመራ ይችላል የሚያስችል ሁኔታ ስለሌለ [illegible] ሲሆን፣ ይህ አባባል [illegible] የዲሲፕሊን ፍርሃት፣ ግለሰብኝነትና ``በማን አንሼ`` ከሚንፀባረቅ ለበታችነት ምንም ሳይገባቸው መሰረት የሌለው ምክንያት ነበር፡፡በተጨማሪም፣ ለነርሱ የኢትዮጵያ አብዮት ገና እጅግ በጣም ሩቅ ሆኖ ይታያቸው ነበር፡፡ከነዚህ የቀኝ አድርባይነትን ያራምዱ ከነበሩት ምሁራን ውስጥ ብዙዎቹ ለጥቂት ጊዜያት በጠባብ ``የጥናት ቡድን`` ውስጥ ቆይተው፣ የየካቲት እንቅስቃሴም ሲመጣ ፍፁም ግራ ተጋብተው ወደመከላሸትና ትግሉን ወደመተው ገብተዋል፡፡አንዳንዶቹም ከ``ግራ`` አድርባዮች ጋር ከፀረአብዮት ሰፈር ተደባልቀዋል፡፡ከየካቲት እንቅስቃሴ ወዲህም መኢሶን ሊመልሳቸው ያደረገው ጥረት ፍሬን አላሰጠም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ``የግራ`` አድርባይነትን ያራምዱ የነበሩት፣ የኢትዮጵያ አብዮት ``ከመብሰልም አልፎ ስለበሰበሰ``፣ የሚፈጠረው ድርጅት ጠንካራ እስኪሆን ሳንጠብቅ፣ መቶ ያህል ሰዎችን ይዘንና ከኤርትራ ግንባሮች፣ ከኢ.ኤል.ኤፍ /እና በሃላም ከፒ.ኤል.ኤፍ/ ጋር ተጠግተን ወዲያውኑ የገሪላ ውጊያን መጀመር አለብን ይሉ ነበሩ፡፡ለነዚህ ወገኖች፣ የኢትዮጵያ አብዮት በአንድ አለት ደርሶ–መልስ የሚከናወን መስሎ ስለታየ፣ ጠንካራ ድርጅትን ለመፍጠር፣ ድርጅቱም በሰፊው ህዝብ ውስጥ ትስስሩንና ፕሮፓጋንዳን አካሂዶ ከዚያም ደረጃ በደረጃ ወደህዝባዊ ጦርነት እንዲያመራ ማቀዱ ``በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ወንጀል መፈፀም`` ነበር፡፡ ``የግራ`` አድርባዮቹ ዛሬ ኢህአፓ በሚል ስም የታወቀውን ድርጅት ፈጥረው እንዳቀፉት ሁሉ፣ አምሳ የማይሞሉ ተዋጊያችን በኤርትራ በረሃ አሰማሩ፡፡ከነዚያ ውስጥ ብዙዎቹ በርግጥ በቆራጥነት ለኢትዮጵያ አብዮት ህይወታቸውን አሳልፈው ለመስጠት ዝግጁ የሆኑ ሃቀኛ፣ ግን የተሳሳቱ፣ ጓዶች ነበሩ፡፡የታሪክ ፍርዱ ሆኖ፣ የየካቲት እንቅስቃሴ በፈነዳና የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል አንዳንድ ድሉቸውን በተቀዳጀበት ወቅት፣ ከነዚህ ጓዶች ውስጥ አንዳንዶቹ ሁኔታውን በተከከለ በመገምገም ሰልፋቸውን ለማስተካከል ሲችሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ አንስየለታለን ባሉት አርሶአደር እጅ እንዲወድቁ ሆኗል፡፡

መኢሶን እንደአንድ ማርክሲስት–ሌኒኒስት ድርጅት ሲቋቋምና እስከዛሬ እየወደቀ እየተነሳ አንድነቱን ጠብቆ ወደፊት ለመራመድ የቻለው፣ በትግል ውስጥ ስለተፈጠረ ነው፡፡በመጀመሪያ ደረጃም እነዚያን የቀኝና ``የግራ`` አስተሳሰቦችን ለማሸነፍ ስለቻለ ነው፡፡መኢሶን፣ የቀኝ አድርባዮችና ``የግራ`` አድርባዮች ድርጅቶችና ቡድኖች የተፈጠሩት በተማሪ ማህበራት አካባቢ ስለሆነ ትግላቸውንም ያስፋፉት በተማሪ ማህበራት ውስጥ ነበር፡፡በአገር ውስጥ እነዚህ መስመሮች በስውር ሲሻኮቱና በፀረፊውዳል ትግሉ አንዳንዴም ሲተባበሩ በውጭ አገር ግን በገሃዱ ሲታገሉ እስከ 1966 ድረስ ቆዩ፡፡

ላለፉት ስድስት አመታት በውጭ አገር የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ውስጥ የተካሄዱትና አሁንም በመካሄድ ላይ ያሉት ሃይለኛ ፖለቲካዊና ርእዮተአለማዊ ትግሎች ዝር ዝር በመኢሶንና በኢህአፓ መካከል የተካሄዱ ትግሎች ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡የታህሳስ 53ን የኩዴታ ሙከራ፣ የተማሪ ማህበራትን ታሪካዊ ሚናና አደረጃጀታቸውን፣ የብሄር ጥያቄዎችን፣ በኢትዮጵያ ያሉትን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በሚመለከቱና በሌሎችም ጥያቄዎች ላይ ሁለቱ ወገኖች ሲፋጩ ቆይተዋል፡፡አንባቢው ዝርዝሩን በተለይ ከአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ጽሁፎች ሊያገኘው ይችላል፡፡በተለይ ግን የየካቲት እንቅስቃሴ ከፈነዳ በሃላ፣ ይህንን እንቅስቃሴ ማን መራው /ሌላትም በሀርዩ ምንድነው/ በሚለው ጥያቄ ላይ፣ በመሬት ለራሹ መፈክር ላይ፣ በፓርቲያች የመመስረት ጉዳይ ላይ፣ በጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትና በሌሎችም የኢትዮጵያ አብዮት ጥያቄዎች ላይ የነበሩት ትግሎች፣ ሁለቱ ድርጅቶች እየተራራቁ እንዲሄዱ አድርገዋል፡፡ከመኢሶን የዚያን ጊዜ ዳተኛነት የተነሳ ከኢህአፓ ጋር ተሰልፈው ከነበሩት ሃቀኛና ከሁሉም የበሰሉ አብዮታውያን ውስጥ ብዙዎቹ ወደድርጅታችን ሊመለሱ የቻሉት በዚህ በከረረ ትግል ውስጥ ነበር፡፡

.../4

ይህም ሆኖ ሳለ፣ በተለይ ከመስከረም አብዮቱ ፍንዳታ በኋላ በነበረው ጊዜ ውስጥ የ
ሁለቱ ድርጅቶች አንድ አይነት መፈክሮች ይዘው መውጣት ከድርጅታችን ያመራር ጉድለት የመነጨ
እንጂ በሁለቱ ያስተሳሰረ ህግ ላይ የተመሰረተ አንድነት አልነበረም።

ይሁንናም፣ በጥር—የካቲት 1967፣ መኢሶን የተራማጆችን ህብረት አስፈላጊነት
በመገንዘብ፣ በድርጅቶቻችንና በኢህአፓ፣ እንደዚሁም በሌሎች ቡድኖች መካከል በከፍተኛ ደረጃ
ውይይት እንዲካሄድ አደረገ። የተራማጆችን የተግባር አንድነት ለመፍጠር፣ በአስተሳሰብም
መቀራረብና ከዚያም ተዋህዶ የወዛደሩን ፓርቲ ለመመስረት፣ መጀመሪያ በኢትዮጵያ ሁኔታ ትን
ተና ላይ፣ በወዳጅና በጠላት መደቦች አሰላለፍ፣ በደርግ ባህርይና በጊዜው አጣዳፊ ተግባሮች
ላይ፣ ከስምምነት ላይ መድረስ ያስፈልግ ነበር። በዚያን ጊዜ ከነበረው ሁኔታ ለመገመት ይ
ቻል እንደነበር ሁሉና ባለፉት ሁለት አመታት ከተፈጠሩት ሁኔታዎች ለማረጋገጥ እንደሚቻል
ሁሉ፣ በምንም ነጥብ ላይ ስምምነት ለማግኘት አልተቻለም። የኢህአፓ ምኞት ፀረ—ደርግ ግን
ባርን ፈጥሮ በተቻለ ፍጥነት የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ ሲሆን፣ መኢሶን ግን ይህንን ስ
ልጣን ሰፊው ህዝብ እንዲይዝ ለማድረግ መታገል ነበር። እነዚህ ሁለት የተራራቁ አላማዎች
በምንም መንገድ ሊቀራረቡ ከለማቻላቸው በላይ፣ ሌላው ቀርቶ ኢህአፓ በጋዜጣችን በሰፊው
ህዝብ ድምጽ ላይ ቀደም ብሎ ጀምሮት የነበረውን የስም ማጥፋት ዘመቻ እንዲያቆምና በፕሪን
ሲፕል ጥያቄዎች ላይ እንዲያተኩር የተጠየቀውን ማሟላት አልቻለም። ስለሆነም፣ ከረጅም ጊዜ
ከንቱ ክርክር በኋላ ውይይቱ ያለንዳች መደምደሚያ እንዲቋረጥ ተደርጓል።

ኢህአፓን በሚመለከተው በኩል በድርጅታችን ውስጥ ሁለት መስመሮች ነበሩ። አንደ
ኛው መስመር የኢህአፓ ሰዎች የተሳሳቱ አብዮታውያን ናቸው፣ በጥንቃቄ ከተያዙና ከተመከሩ
ሊታረሙ ይችላሉ፣ ቀስ በቀስም አብረን የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር እንችላለን የሚል ነበር።
ሁለተኛው ደግሞ ሰዎቹ ንኡስ ከበርቴው ሪቮሉሽኒዝም* ያጠቃቸው፣ ጥራዝ ነጠቆች፣ በሳይንሳዊ
ትንተና ፈንታ በአሉባልታ፣ በመንደር ወሬና በስሜት የሚመሩና ስለዚህም ቁጣቸውን ያገሪቱን
ሁኔታ በትክክል ሊያዩት የማይችሉ ስለሆኑ፣ የሃሳብ ተኩስ ተከፍቶባቸው ይጋለጡ የሚል ነበር።
እንደዚያም ሆኖ ግን፣ ድርጅታችን በጥር 67 ውይይትን ለማድረግ መሞከሩ ትክክለኛ እርምጃ
እንደነበር ግልጽ ነው። ኢህአፓን ለመመለስ እስከመጨረሻው መታገል ተገቢ ነገር ከመሆኑም
በላይ፣ በጊዜው የነበረውና ዛሬም ያለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ባንድነት ሊሰበሰብ የሚችለውን
ሀይል ሁሉ የማስተባበርን ግዴታ ከሃቀኛ ተራማጆች ይጠይቃልና።

መደብ ከገመድ ይጉተታል እንደሚባለው ሁሉ፣ ኢህአፓ የመደብ ባህርዩን ሊለውጥ
አልቻለም። ከግንቦት 67 ጀምሮ በክረምቱ የኢሰአማንና የመምህራን ማህበርን አመራሮች አፀ
ናብያ በቁጥጥሩ ስር ካደረገ በኋላ፣ ባንድ በኩል በነዚህ "ውጤቶች" ስለሰከረ፣ በሌላ
በኩል ደግሞ በመስከረም 2/68 ደርጉ አንድ እራሱን የቻለ የወታደር ፓርቲ ያቋቁማል የሚል
ወሬ ስለነበር፣ ደርጉን ለመቅደም ሲል፣ ፕሮግራሙን አወጀ። መጀመሪያ የመምህራን ማህበር፣
ከዚያም ኢሰአማ በጀብደኝነትና በድንገቴ የተሞሉ ውሳኔዎችን እንዲያሳልፉ በማድረግ አጋፈጧ
ቸው። በመስከረም ፀር 68፣ ጠቅላላ የስራ ማቆም እርምጃን አስወስዳለሁ ብሎ በመደንፋት፣
በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰራተኞች ላይ እንዲተኩስና ሰባት ሰዎች እንዲሞቱ፣ በርከት ያሉት
እንዲቆስሉ፣ ባዲስ አበባና ባካባቢዋ ያስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲታወጅና ብዙ የኢሰአማና የ
መምህራን አባሎች እንዲታፈሩ ለማድረግ በቃ። በነዚህ ድርጊቶች የደርግን "ፋሺዝም" ለ
ማስመስከር የቻለ መሰለው። በዚህ ሁኔታ፣ ድርጅታችን ከግንቦት 67 ጀምሮ ሂሶችን በኢህአፓ
ላይ ሲሰነዝር ከቆየ በኋላ፣ በመስከረም 68 የድርጅቱን ፀረ አብዮታዊነት ማጋለጥ ጀ
መረ።

ኢህአፓ በ1967 መጨረሻ እና በ1968 የወዛደሩን፣ በተለይም የመምህራንን እና
የወጣቶችን እንቅስቃሴዎች በሙሉ በክሎአቸዋል። የመሬት ለአራሹና የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች
አዋጆች ከወጡ በኋላ በተለይ፣ ከንኡስ ከበርቴው ክፍል ብዙ ደጋፊዎችን ለማግኘት ችሎአል።
በተረፈም፣ የአብዮት እርምጃ የመታቸውና ያስደነገራቸው የህብረተሰባችን መደቦች ሁሉ — የመ
ሬት ከበርቴው፣ የቢሮ ከበርቴውና የቀኝ ክንፍ ንኡስ ከበርቴው— በኢህአፓ "ጠበቃቸውን"
ወይንም "ነገረፈጃቸውን" ለማግኘት ችለዋል። የኢህአፓ መፈክሮችና ቅስቀሳዎች የወደቁትን
መደቦች ሁሉ የሚያስለፉ፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ሌሎችንም ቀልባሽ ሃይሎችን ሁሉ የሚስቡ ስለሆኑ፣
ይህ ፀረ አብዮታዊ ድርጅት ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊጠናከር ችሎ ነበር።

"የመደቦች ትግል በፈረንሳይ" በሚባለው ጽሁፉ ውስጥ፣ ካርል ማርክስ፣ "...ንኡስ ከበርቴው በከበርቴው ላይ ያለውን አብዮታዊ አመለካከት ይዞ የሚቆየው ወዛ
ደሩ ከኋላው እስከተሰለፈ ድረስ ብቻ ነው" ብሏል። ወዛደሩ ለራሱ የመደብ ጥቅም ነቅቶ

---

* ሪቮሉሽኒዝም የቀኝ ክንፍ ንኡስ ከበርቴ ርእዮተ አለም ሲሆን፣ እርሱም ጊዜንና
ሁኔታን ከሳይንሳዊ ሶሻሊዝም አንፃር ሳይመረምሩ፣ አብዮት—አብዮት
እያሉ አይንን ጨፍኖ መሯሯጥን ያስከትላል። የንኡስ ከበርቴውን የ
ቅብዝብዝነት ባህርይ ያንፀባርቃል። የሪቮሉሽኒዝም ነባራዊ አላማ
የወዛደሩን እንቅስቃሴ በማጋፈጥ ማስመታትና ወዛደሩን መበታተን
ተስፋ ማስቆረጥ ነው።

ከንጉሡ ከበርቴው ሥር ሳይሆን ከፊቱ የተሰለፈ አለት የንጉሡ ከበርቴው ፀረከበርቴነት ያከትማል፡፡ ንጉሡ ከበርቴው መክዳት ይጀምራል፡፡ በ1967 እና 68 የኢትዮጵያ አብዮት ያገኛቸው አንዳንድ ድሎች ስር ሰደረገ ህዝብ ወደፊት መድረክ የሚያመጡት መሆናቸው ሲሰማው፣ በሃይለ ስላሴ ፊውዳሊስት ስርአት ላይ "አብዮታዊ አመለካከት" የነበረው የቀኝ ክንፍ ንጉሡ ከበርቴ ተደናግጦ ወደፀረአብዮት በፈር መንገስገስ የግድ መምረጥ ነበረበት፡፡ የኢህአፓ፣ የ ጥድ እሳት መንበግበግ የሚገልፀው ይህ እውነት ነው፡፡

አሁን ባለንበት ወቅት፣ ከአንድ አመት በላይ ከፈጀ የከረረ የፖለቲካ ትግል - በኋላ፣ ድርጅታችንና ሌሎችም ማርክሲስት-ሌኒኒስት ቡድኖች የንጉሡ ከበርቴውን ደገፊ ቡድን በፖለቲካ ደረጃ ሲደመስሱት ችለዋል፡፡ ስለዚህም ነው፣ ይህ ፀረአብዮታዊ ድርጅት እውነተኛ መልኩን በማሳየት፣ አብዮታውያን ቀደም ብለው እንደተነበዩት ሁሉ፣ ወደነፍሰገዳይነት የተዘዋወረው፡፡ የ[illegible] ሰራው ሁሉ የኢትዮጵያን ሁኔታ ለቀለበሳ ሙቻቸት እንደነበር የሚያስከረው ዛረ ከ[illegible] ከሌሎችም አድሃሪ ሃይሎች የሚራሱና የማቴሪያል ድጋፍ ማግኘቱ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ግን ከጠቅላላ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ክስረት አያድነውም፡፡ ኢህአፓ በገዶቻችን ላይ የፈፀመውንና የሚፈጽመውን ግድያ እንበቀላለን፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ከፒታሊዝም ጋር በሚያደርጉት ትግል ውስጥ፣ እነርሱን መስሉ የተደበቁ [illegible] አድሃሪያን የውስጥ አርበኞች [illegible] ይደመስሱታል፡፡

III

በየካቲት 66 የፈነዳው የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ወደር ያልነበረው እንቅስቃሴ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ መደቦች ሁሉ ከዳር እስከ ዳር የቀሰቀሰና በትግል አፍላ ውስጥ የጨመረ እንቅስቃሴ ስለነበር፣ ከቀደሙት እንቅስቃሴዎች ሁሉ በጥልቀቱና በስፋቱ አንፃር የተለየ ነበር፡፡ በለፉት ሶስት አመታት ውስጥ፣ ይህ እንቅስቃሴ ፈጽሞ ያልታለሙ ድሎችን ያስገኘ ከመሆኑም በላይ፣ አሁንም እየወደቀ እየተነሳ፣ እያሉ መሰናክሎችን እያለፈ፣ ወደፊት በመገስገስ ላይ ይገኛል፡፡ በርግጥ ይህ አብዮት አሁንም ገና ከተቀለበሰ ሊድን ይችላል ከሚባልበት ደረጃ ላይ አልደረሰም፤ ሰፊው ህዝብ የአብዮቱን ጠላቶች ደምስሶ የመንግስትን ስልጣን ገና አልያዘምና፡፡

በብዙ የድርጅታችን ጽሁፎች ተደጋግሞ እንደተነገረው፣ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች የየካቲት እንቅስቃሴ በፈነዳበት ወቅት የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ አልተዘጋጁም ነበር፡፡ እንቅስቃሴው ግብታዊ ከመሆኑም ሌላ፣ ይህንን ግብታዊነት ወደተቀናበረ ትግል ለመለወጥ የሚችል፣ ሰፊው ህዝብ በመሪነት የተቀበለው አብዮታዊ ድርጅት አልነበረም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ገዥ መደቦችም፣ ማለትም ፊውዳሉ መደብና የቢሮ ከበርቴው፣ እንቅስቃሴው ይህን ያህል ርቀት የሚሄድ አልመሰላቸውም ነበር፡፡ በተለይም የተማሪ መሳፍንቶችና የዘውዳዊ ቢሮክራሲያዊ ከበርቴዎችን ስልጣን ለማደላደል ተቋቁሞ የነበረው የእንዳልካቸው መንግስትና የርሱ መሪ ደጋፊ የነበረውም የሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም፣ በንቅስቃሴው ባህርይ ላይ ያልነቃበት ስለነበር፣ የእንዳልካቸው መንግስት፣ እንደአክሊሉ መንግስት ሁሉ፣ ወዲያውኑ ለወገድ ችሎአል፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ የመንግስትን ስልጣን ከእጁ ከሚያስገባበት ሁኔታ ላይ አልነበረም፡፡ ይህንን ለማድረግ የሚያስችለው፣ ለመንግስት ስልጣን ያዘጋጀው፣ ትግሉን አቀነባብር የሚመራ ድርጅት አልነበረውም፡፡

የማንኛውም አብዮታዊ እንቅስቃሴ ዋና ጥያቄ የመንግስት ስልጣን ጥያቄ መሆኑ፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብም የመንግስትን ስልጣን ከሚይዝበት ሁኔታ ላይ እንዳልነበረ ግልጽ ሆና ሳለ፣ በሚያዝያ 1966፣ ለመጀመሪያ ጊዜ "ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት" የሚለውን መፈክር አውጥቶ አሰራጨ፡፡ በዚህ መፈክር ላይ በቅድሚያ በድርጅቱ ውስጥ ሰፊ ውይይት ተካሄዶበትም ነበር፡፡ "ለጥቂት ቀናት የመንግስት ስልጣን በአየር ላይ የተንጠለጠለችና የሚቀልብት የጠፋ ከስ ስለነበረች" በማለት፣ ደግሞም በሚያዝያ ወር የእንዳልካቸው መንግስት የያዘው አዝማሚያ ቢቀጥልና ስልጣኑን ቢያደላድል ኖሮ አብዮታዊው እንቅስቃሴ ከባድ የሚመጣ ስለነበር፣ የጊዜውን አጣዳፊነት በመመልከት፣ ድርጅታችን ማእከላዊ አመራር በጊዜ ስልጣኑ መፈክሩን አወጣው፡፡

ወዲያውኑ ድርጅቱ ውስጥ፣ በአገር ውስጥና ሆነ በውጭ አገር፣ ተቃዋሚ ድምጾች መሰማት ጀመሩ፡፡ በነሐሴ ወር 66 በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ጉባኤ ላይ የኢህአፓ ደጋፊዎች የመኢሶንን መፈክር ይዘው ሲከራከሩ፣ የመኢሶን ደጋፊዎች ደግሞ መፈክሩን ተቃውመው እስከመከራከርና እስከማሸነፍ ደርሰዋል፡፡

የየካቲትን እንቅስቃሴ በሀርይ የድርጅታችን አንዱ ክፍልም ሆነ የንጉሡ ከበርቴው ደጋፊ ቡድን፣ ገዥ መደቦችም ሆኑ ኢምፔሪያሊዝም በጊዜው በተከከለ ያልተረዱት፣ በትግሉ ውስጥ የመደቦች አሰላለፍ ለጥቂት ወራት ተዘበራርቆ ስለነበር ነው፡፡ በድርጅታችን ውስጥ

.../6

"ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ተቃዋሚ ክፍል፣ ይህንን ዝብርቅርቅ ሁኔታ ዘለቄ በመመልከት፣ እንቅስቃሴው ከመጀመሪያው የቡርዧ ዲሞክራቲክ አብዮትን መልክ የያዘና በንኡስ ከበርቴው የተመራ መሆኑን በማመን ሲከራከር፣ ደጋፊዎቹ ግን እንቅስቃሴውን የጀመረውና የመራው ሰፊተኛ ዲሞክራሲያዊ የሆነው የኢትዮጵያ ወዛደር መደብ ነው" እስከማለት ደርሰው ነበር:: አድሃሪ መደቦችና ኢምፔሪያሊዝም በበኩላቸው በተለመደው አባባል አመለካከታቸው የንቅስቃሴውን ምንጭ ይፈልጉ የነበረው በጥቂት "ቀንደኛ መሪዎች"፣ በግለሰቦች ዘንድ ስለነበር፣ ሊረዱትና ከቁጥጥራቸው ስር ሊያውሉት ፈጽሞ አልቻሉም::

የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መፈክር ሊወረወር የቻለው የየካቲትን እንቅስቃሴ ባህርይም ካለመረዳት የተነሳ ሲሆን፣ በመሰረቱ፣ እስከ የካቲት 67 ድረስ፣ መኢሶን ይህንን መፈክር ሲያራምደው ቆይቷል::በየካቲት 67 በአመራሩ ውስጥ የነበረው ክርክር ለድርጅቱ አንድነት የሚያሰጋ በሆነበት ወቅት፣ ለጊዜው ድርጅቱ መፈክሩን ማራመዱን እንዲያቆምና ሰፊ ውይይት በድርጅቱ ውስጥ እንዲደረግበት ተወሰነ::ውይይቱ ተካሄዶ መፈክሩ ውድቅ ሲሆን፣ በግንቦት 67 መኢሶን በይፋ መፈክሩን ማጋለጥ ጀመረ::እራሱ ያወጣውንና ለደገፈው ቡድን ያስጨበጠውን መፈክር ተገንቶ ለመሸነፍ ከአመት በላይ ጊዜንና ብዙ ጉልበትን ጠይቋል:: /በነገራችን ላይ፣ የንኡስ ከበርቴው ደጋፊ ቡድን እኛኝ ብሎ ይዞት የቆየውን "የምርጥ መካንኖች መንግሥት" የሚለውንም አጠራር ያስታቀፈው ፀሐፊ፣ የመኢሶን ክፍል ነበር!/

የየካቲት 66 የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ በፈነዳበት ወቅት፣ ምንም እንኳን ስሙን በይፋ ባይገልጥም፣ ድርጅታችን ከነበሩት ቡድኖች ሁሉ የበለጠ ጥንካሬና ተሰሚነት የነበረው ከመሆኑም በላይ፣ የቀሩት ሁሉ፣ ኢህአፓንም ጨምሮ፣ ከርሱ ጋር የተያያዙ ነበሩ::እርሱ ነበር የሚመራቸው ለማለት ይቻላል::ስለሆነም፣ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" የሚለውን መፈክር ሲያወጣ ሁሉም በጭፍን ጉደል ተቀብለውታል::በጊዜው ተቃውሞን አሰምቶ የነበረው የአብዮት ቡድን ሲሆን፣ እርሱም መፈክሩን የተቃወመው መፈክሩ የሚያስከትላቸውን ቲዎሪያዊና የተግባር ትርጉሞቹን በመገምገም ሳይሆን፣ ቡድኑ "ጊዜው የመሳሪያ ትግል ነው" በሚል ሰበብ ወደ ቴሮሪዝም ለመሸጋገር አቅዶ ስለነበር ነው:: የአብዮት ቡድን ብዙም ሳይቆይ ከኢህአፓ ጋር መዋሃዱና የሁለቱም ቡድኖች በ1969 በግድያ መሰማራት ከመጀመሪያውም የነበራቸውን የመደብ ጠባይ —የንኡስ ከበርቴ ፋሺስትነታቸውን— በሚገባ አረጋገጡለት::

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከ1966 በፊት፣ በስልጣን ጥያቄ፣ በብሄር ጥያቄ ገለጻ ያልነበረ አቋም የነበራቸው አንዳንድ ምሁራንና ንኡስ ቡድኖች ማርክሲዝምን ለማስፋፋት ከመኢሶን አባላት ጋር ተባብረው፣ በስውርና በግልጽ በሚሰሩ የጥናት ክበቦችና የሙያ ማህበሮች ውስጥ ሲሰሩ ቆይተው ነበር::አንዱ አከራካሪ አቋማቸው ጥያቄ ወታደሮችን ይዞ ኩዴታ ለማድረግ የሚመኙ መሆናቸው፣ ሌላው በኤርትራ ጥያቄ ላይ ፍፁም ተምክህተኝነትን ማሳየታቸው ነበር::እንደዚሁም ደግሞ ሌሎች የነዚህ ተቃራኒ የሆኑ፣ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል ከብሄረሰብ አንፃር ብቻ የሚመለከቱ፣ ጠባብ ብሄርተኞች ነበሩ::እነዚህ ወገኖች፣ አንዳንዶም የመኢሶን አባላትና ደጋፊዎች ጨምረው፣ ከመኢሶን ርቀው በ1967 እና 68 ውስጥ አዳዲስ ቡድኖችን እስከመፍጠር ደርሰዋል::

"ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" የሚለው መፈክር ድርጅታችንን ከነበረው የመሪነትና የጥንካሬ ቦታ ወደታች እንዳቀረቀረው ባለፉት ሁለት አመታት የተደረጉት ትግሎች በሚገባ አሳይተዋል::አንዳንድ ሰዎች ይህ መፈክር ስህተተኛ ቢሆንም በጊዜው የመለዮ ለባሹንና በመቀሳቀሉም የሰፊውን ሕዝብ ትግል በማፋፋም የሃይለስላሴን መውደቅ እስከማስከተል ደርሶአል ይላሉ::እንደውነቱ ከሆነ ግን፣ የሰፊውን ሕዝብና የመለዮ ለባሹን ትግል ያፋፋመው መፈክሩ እራሱ ሳይሆን፣ በመቀሳቀሉ በእንዳልካቸው መንግሥትና በሚካኤል እምሩ መንግሥቶች ላይ፣ ከዚያም በሃይለስላሴ በራሱ ላይ የነበረው ተቃውሞ ነበር:: ሃይለስላሴን በማጋለጥ በኩል በተለይ ድርጅታችን ከፍተኛ ሚናን ተጫውቶአል::

እንዳልካቸው ስልጣን ላይ ሲወጣ የተሰነዘረው "የእንዳልካቸው መንግሥት ይውደቅ." የሚለው መፈክር ትክክለኛ እንደነበር ምንም ጥርጥር የለውም::እንደዚሁም እንዳልካቸው ወድቆ በሚካኤል እምሩ ሲተካ፣ "ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም!" በማለት የርሱንም መንግሥት መውደቅ መጠየቅ ትክክለኛ ነበር::ነገር ግን እነዚህን መፈክሮች ሊከተሉ የሚገቡ ሌሎች መፈክሮች "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይታወቁ! ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ይቋቋም!" የሚሉት ነበሩ::በተለይም በመጋቢትና በሚያዝያ 66 በየቦታው ሕዝባዊ ኮሚቴዎች መቋቋም በያዙበትና በመኢሶን አንቀሳቃሽነት የመንግሥት መስሪያ ቤቶችን አጠቃላይ ኮሚቴ ለማቋቋም በቻለበት ወቅት፣ ዋናው ትግል ማተኮር የነበረበት ወዲያውኑ የመንግሥትን ስልጣን ለመያዝ በመሞከር ላይ ሳይሆን በሰፊው ሕዝብ ነፃ የመደራጀት መብት ላይ እንደነበር፣ ዛሬም እንኳን ያለንበት የትግል ደረጃ እራሱ ይመሰክራል::አሁንም ገና ሰፊው ሕዝብ ይበልጥ መደራጀት አለበትና::

በ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' ላይ የተደረገው የመስጦር ትግል፣ በተለይም ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ከተቋቋመ በሗላ፣ ከደርጉ የመደብ ባህርይ ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነበር::ይህንን ጥያቄ በሚመለከተው በኩል፣ ዋናው ጥያቄ ''ደርጉ በሲአይኤ የሚመራ የምርጥ መኮንኖች ቡድን ነው ወይንስ የአገር ወዳድና የለውጥ ፈላጊ ንኡስ ከበርቴዎች ሸንጎ ነው'' የሚለው ነበር::በፊተኛው አስተሳሰብ ከተሄደ፣ ደርጉ፣ በ1968 ኢህአፓ እንዳለው ሁሉ፣ የኢምፔሪያሊዝምን፣ የፊውዳሊዝምና የቢሮክራቲክ ከበርቴውን መደቦች መደቦች ጥቅም የሚጠብቅ ቡድን ስለሆነ እስከመጨረሻው ለንዮጋው ይገባል ማለት ነው::በሁለተኛው ከሆነ፣ ደርጉ የንኡስ ከበርቴውን መደብ የግራ ክንፍ የሚወክልና ቢያንስ ለዲሞክራሲያዊ ለውጦች የሚታገል ሃይል ይሆናል::ስለሆነም፣ ከርሱ ጋር ጊዜያዊ ወዳጅነትን ለመፍጠር ይቻላል ማለት ነበር::

ደርጉ በሲ.አይ.ኤ. የሚመራ የምርጥ መኮንኖች ቡድን ነው የሚለውን አስተሳሰብ ከሰከተሉት ነገሮች አንዱ የኢትዮጵያን ሰራዊት ያሰለጠኑ ያስታጠቁ፣ የሚቆጣጠሩት አሜሪካኖች መሆናቸው በደርጉ ውስጥ ብዙ መኮንኖች በዙያቸው በአሜሪካን አገር የሰለጠኑ መሆናቸው ነበር::በተጨማሪም የጥቂት የደርጉ አባላት መኮንኖች በውስጡ ካንዳንድ አሜሪካኖች ጋር መገናኘትና የደርጉ በኢምፔሪያሊዝም ላይ ወሳኝ አቋም ይዞ መቆየት ጥርጣሬውን አጠናክርታል::በርግጥ ከ[illegible] ጋር የተደረገ ግንኙነትና [illegible] የነበራቸው እንደነበሩ ሃብቱ [illegible] አሉ[illegible] ሌሎችም ከፍተኛ [illegible] በወቅቱ ሰው የመለቀቁ ሰባቱ እንቅስቃሴና የደርጉ አመጣጥ፣ ደርጉ [illegible] እስከዛሬ አልፎ አልፎ መቀበሉ፣ በተራማጆች በኩል በደርጉ ላይ የነበረውን ጥርጣሬ ሊቀንስ በተገባው ነበር::

ደርግ ከተቋቋመበት ከሰኔ 1966 እስከ የካቲት 67 ድረስ የነበረው የደርጅታችን መሪ አስተሳሰብ በቀላሉ ጉደል በጥርጣሬ ላይ የተመሰረተ ስለነበር፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ በርከት ያሉ የፖለቲካ ስህተቶች ተፈጽመዋል::በሰኔና በሃምሌ ወሮች ደርጉ ከተራማጆች የፖለቲካ አስተሳሰብ ድጋፍን ይጠብቅ በነበረበት ወቅት፣ አስተያየቶችን በፖስታ እስከመጠየቅ በደረሰበት ወቅት፣ መኢሶን ይህንን ድጋፍ ሊያቀርብ ሲችል፣ ደርጉን በጥርጣሬ በመመልከት ስለሸሸውና ከ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት'' ሌላ ሊያናርብለት ያዘጋጀው ተገባራዊ አሳብ ስላልነበረው፣ አንዳንድ ሪፎርሚስቶችና አድሃሪዎች የበለጠ ተደማጭነትን ለማግኘት ችለው ነበር::መኢሶን የእድገት በህብረት ዘመቻን አሳብ ሙሉ በሙሉ ደግፎ በመውጣት፣ አመራርን በመያዝና አብዮታዊ አስተሳሰቡን በዚያ አማካኝነት ለመላ ኢትዮጵያ ለማድረስ ሲችል፣ ለአሳቡ ሙሉ ድጋፍን ነፍጎ አመራሩን ለሌሎች ተተሰል::እነዚህና ሌሎችም የተሳሳቱ የፖለቲካ እርምጃዎች የፈለቁት ከተባሳተ የደርግ ባህርይ ትንተና ሲሆን፣ እነዚህ እርምጃዎች ድርጅታችንን ጎድተው፣ ለደገፊዎች መስፋፋትና ለሌሎችም አድሃሪዎች መንገዱን አመቻችተዋል::

በታህሳስ 1967፣ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት የታወቀውን የሶሻሊዝም መመሪያውን ያወጣው በሃቀኛ ተራማጆች ተጽእኖ ሳይሆን፣ በሪፎርሚስቶች ተጽእኖ ስር ሆኖ ነበር::የመመሪያው መውጣት እራሱ ትልቅ እርምጃ ሆኖ ሳለ፣ በተለይ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የፓርቲን ጉዳይ በሚመለከተው በኩል፣ መመሪያው ፍፁም ስህተኛ ነጥቦችን ይዞ ነበር::ይሁንናም፣ በጥር 1967፣ ከደርጉ አካባቢ የተባለውን አንድ ፓርቲ ስለመፍጠር ጉዳይ እንዳጋጠሚ የድርጅታችን አንዳንድ ጓዶች ጠርተው አሰብ ተጠይቀው ነበር::አዘጋጆቹ እነዚህ ጓዶችና ሌሎችም ተራማጆች በደርጉ ዙሪያ ተሰብስበው የተባለውን ፓርቲ እንዲፈጥሩ ወደጠየቁ ነበር::ይህ አጋጣሚ በድርጅቱ አመራር ውስጥ በደርጉ ባህርይ ላይ የነበረውን ክርክር ከማፋፋሙም በላይ፣ በኛና በደርጉ መካከል መናር ስለሚገባው ግንኙነት፣ ደርጉን እንዴት መመልከት አለብን በሚለው ጥያቄ ላይ ትግሉን አስከተለ::ስለሆነም፣ ከብዙ ክርክር በሗላ፣ ባንድ በኩል ለደርጉ የፖለቲካ አስተሳሰብና ድርጊቶች በተቻለ መንገድ ሁሉ አብዮታዊ አዘማሚያ እንዲይዝ ትግል ማድረግ እንዳለብን ሲታመን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ የደርጉን ፀረ ዲሞክራሲያዊ ''ያንድ ፓርቲ'' አሳብ ለማስወገድና ለዲሞክራሲያዊ መብቶች በሰፊው ቅስቀሳ ለማድረግ ተወሰነ::

እንደሚታወሰው በጥር 1967፣ በኤርትራ፣ በተየጊ ገንባርኛ በኢትዮጵያ ሰራዊት መካከል ሃይለኛ ግጭት ተደርጎ ነበር::ድርጅታችን ከተፈጠረባት ወቅት ጀምሮ የኤርትራን ህዝብ ትግል ደግፍአል::ይህንን ለዲሞክራሲና ለእኩልነት የተደረገውን ትግል ይደገፍ እንጂ፣ የማንኛውንም የኢትዮጵያን ብሄረሰብ ከንጉስ ነገስቱ መንግስትም ሆነ ከሌላ መንግስት እስከ መገንጠል ያሉቸውን መብት ይወቅ እንጂ፣ መኢሶን የኢህአፓን አድርባይነት በመከተል የገንባርችን የበላይ ተጠባባቂነት ፈጽሞ አልተቀበለውም::በጥር 67፣ በኢትዮጵያ ውስጥና ባካባቢው የሃይሎች አሰላለፍ በሃይለስላሴ ዘመን ከነበረው አሰላለፍ ፍፁም ተለውጦ ነበር::በጥር 67ና ዛሬም የኤርትራ ገንባርች በደርጊታቸው ከ...ኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች ጋር መሰለፋቸውን ማሳየት ባስፈለገበት ወቅት፣ የደርጅታችን አመራር በገንባርቹ ላይ ምንም አይነት ሂስ ማቅረብ አያስፈልግም የሚል አቋም ነበረው::በኤርትራ ጉዳይም ላይ ሰፋ ያለ ክርክር ከተደረገ በሗላ፣ በየካቲት 67፣ ድርጅታችን፣ ባንድ በኩል የደርጉን ''የኢትዮጵያ አንድነት ፍፁምነት'' የጉልበተኛና የትምክህተኛ አስተሳሰብ በመቃወም፣ በሌላ በኩል ደግሞ የገ...

.../8

ገባርቻን "የኢትዮጵያን መበታተን ቲያሪ" በማጋለጥ፣ ለኤርትራ ችግር የሰላማዊ መፍትሄን ሀሳብ አቀረበ:: የመኢሶን ሀሳብ መጀመሪያ የተኩስ ማቆም ስምምነት በውይይት እንዲገኝ፣ ከዚያም የሶስት-አራት አመታት ሰላማዊ ሁኔታ ተፈጥሮ የኢትዮጵያና የኤርትራም ህዝቦች በመገንጠሉ ጥያቄ ላይ ሰፊ ዲሞክራሲያዊ ውይይትን እንዲያደርጉና ከዚያ በሗላ የኤርትራ ህዝብ የገዛ እድሉን እንዲወስን ነበር:: ለመገመት እንደሚቻለው ሁሉ፣ ደርግም ሆነ ገንባርቻ በዚያን ጊዜ የዚህ አይነቱን አስተሳሰብ ለመከተል ስላልቻሉ የኤርትራ ችግር ወደመፍትሄው ባይቀርብም፣ ከዚያ ወዲህም ቢሆን ድርጅታችን ለሰላማዊ መፍትሄ እንደታገለ ነው::......

ጊዜያዊ ወታደራዊ-መንግስት ከተቋቋመበት ወቅት አንስቶ እስከየካቲት 67 ድረስ፣ ይህንን መንግስት በሚመለከተው በኩል፣ የመኢሶን መመሪያ፣ እንደደንፊያቹ መመሪያ ሁሉ፣ "የማያቋርጥ ተያውቅ" ነበር:: ከደንፊያቹ በዚህ በኩል የሚለየው ደርጉ የሚወስዳቸውን እንቅስቃሴ ተራማጅ እርምጃዎች በጽሁፎቹ መደገፉ ነበር:: በመንግስት ጥያቄ ላይ ግን፣ ከተማሪ ማህበራት ሰምድ የተወረሰውንና "ህጋዊ ትግል" ን ፈጽሞ የማያውቀውንና መመሪያ የመለወጫው ወቅት እንደመጣ ድርጅታችን፣ በተለይም አመራሩ፣ አልተረዳውም ነበር:: በሌላ በኩል ግን፣ በዚሁ ጊዜ ውስጥ፣ "የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት" ተያያዥ የድርጅታችን ክፍሎች ሰንዝረው የነበረው "ወደ ሂስ ድጋፍ" ወይንም "የአብዮታዊ ሂስ" መመሪያ በድርጅቱ ውስጥ መስፋፋት ይዞ ነበር:: ይህንኑ መመሪያ የተመሰረተው የደርጉን አመጣጥ፣ የወሰዳቸውን እርምጃዎችና ወደፊትም ሊኖረው የሚችል የአብዮታዊ ሚና ግምገማ ላይ ሆኖ፣ ባንድ በኩል የደርጉን ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት አዝማሚያዎችና በሌላ በኩል ደግሞ በደርጉና በሰፊው ህዝብ መካከል ያለውን ቅራኔ በመመልከት፣ ይህንኑ ለጊዜው የሁለተኛ ደረጃን ለመያዝ የሚችል መሆኑን በማመን ላይ ነበር:: በየካቲት 67 ይህንኑ መስመር በድርጅታችን ውስጥ የአሸናፊነቱን ቦታ ለመያዝ ችሏል::

"የአብዮታዊ ሂስ" መመሪያ የመሬት አዋጁ ከስራ ላይ ለማዋልና በእድገት በህብረት ዘመቻ ጥሪ መኢሶን ለባዊ ተሳትፎን እንዲያደርግ ሰፊ በር ከፍቷል:: ይህ ብቻ ባይሆን፣ የደርጉ "ያንድ ፓርቲ" ሀሳብ ቀስ በቀስ ተለውጦ፣ አንዱ የህዝብን መደራጀት የሚያገዝና የሶሻሊዝምን ፍልስፍና የሚያስፋፋ ተቋም እንዲፈጠርና መኢሶንም ህጋዊ ትግሉን እንዲያፋፍመው ለማድረግ የተቻለው፣ በድርጅታችን ውስጥ ይህ የመስመር ለውጥ ከተደረገ በሗላ ነበር:: ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮት የያዘውን አቅጣጫና የደረሰበትን ደረጃ ስንመለከት፣ ይህ የመስመር ለውጥ ለአብዮቱና ለድርጅታችን ያመጣውን ጥቅም በግልጽ ለማየት ይቻላል::

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በየካቲት 66ም ሆነ በመስከረም 67 የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ ያልቻለው ትግሉቻን አቀናብሮ የሚመራ ጠንካራ ድርጅት ስላል ነበረ ነው:: በርግጥ መኢሶንና ሌሎችም የግራ ቡድኖች ነበሩ:: ነገር ግን ሁሉም ገና ለጋ የሆኑ፣ በሰፊው ህዝብ ውስጥ ያልተተከሉ የምሁራን ቡድኖች እንጂ እንኳም የወዛደሩን ፓርቲ ከሩቅም የሚመስል ድርጅት አልነበረም:: ስለሆነም፣ የወዛደሩን ፓርቲ በመፍጠር ጥያቄም ላይ በመኢሶን ውስጥ የመስመር ልዩነት ነበር:: የመጀመሪያው መስመር መኢሶንና ሌሎችም የተራማጆች ቡድኖች ባንድ ላይ ሆነው አንድ ሰፊ ዲሞክራሲያዊ ድርጅትን ካቋቋሙ በሗላ፣ ከዚህ ድርጅት ውስጥ የወዛደሩ ፓርቲ ይወጣል ሲል፣ ሁለተኛው ደግሞ መጀመሪያ በተራማጅ ቡድኖች መካከል ህብረትና መቀራረብ እንዲፈጠርና ከዚያም ወደውህደት በመድረስ የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር ይቻላል የሚል ነበር:: ከህዳር 67 እስከየካቲት 67 ድረስ በዚህ ነጥብ ላይ ሰፊ ውይይት ከተደረገ በሗላ፣ ይህኛው መስመር ሊፀድቅ ችሏል፣ በጊዜው በነበረው "የተራማጆች ህብረት" በተባለው ጋዜጣ ላይ በግልጽ ሊወጣ በቅቷል::

የየካቲትን እንቅስቃሴ ባህርይ፣ የመንግስትን ስልጣን ጥያቄ፣ በደርጉ ላይ ሊኖረን ስለሚገባን አቋም፣ ከግራ ድርጅቶች ጋር ሊኖረን ስለሚገባው ግንኙነትና ስለወዛደሩ ፓርቲ አፈጣጠር፣ እንደዚሁም በሌሎች የአብዮቱና የጊዜው ጥያቄዎች ላይ በመኢሶን ውስጥ የነበረ የመስመር ትግል ነበር:: በየካቲት 66 ወዲህ በተደረገው ትግል ውስጥ፣ መኢሶን አንዱ ታላቅ የወደፊት እርምጃን ያደረገው፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ ተጀምሮ በስመቱ፣ በየካቲት 67 የያዘው አዲስ መስመር ነበር:: ከየካቲት 66 እስከ መስከረም 2/67 ድረስ፣ ድርጅታችን በነበረው አቋም፣ እንደሌሎቹ ድርጅቶች ሁሉ፣ ለሃይለስላሴ መንግስት መውደቅ የሚደረግ አስተዋጽኦን አድርጓል:: ከመስከረም እስከየካቲት 67 ድረስ ግን፣ የእንቅስቃሴውንና የደርጉን ባህርዮች፣ የወዳጅንና የጠላትን ወደቦች ሃይሎች በመገምገም በኩል፣ የጊዜውን አንገብጋቢ ጥያቄዎች በመረዳትና ትክክለኛ መፈክሮችን በማንሳት በኩል፣ እንደዚሁም በሌሎች መሰረታዊ ጥያቄዎች ላይ ድርጅታችን ስህተተኛ መስመር እንደነበረው በስራው አሳይቶአል:: ስለሆነም፣ በየካቲት 67 የመስመር ለውጥ ሲደረግ፣ ከርሱም ጋር የማእከላዊ አመራሩ ለውጥ እንዲደረግ የግድ ነበር:: እነዚህ ለውጦች በመደረጋቸው መኢሶን ተጠናክሮ ለኢትዮጵያ አብዮት የተሻለ አስተዋጽኦን ለማድረግ ችሏል::

.../9

መሰረታዊ በሆኑት የኢትዮጵያ አብዮት ጥያቄዎች ላይ የመስመር ለውጥ ሲደረግ፣
መኢሶን ድርጅታዊ አንድነቱን ሊጠብቅ ችሎአል::ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት /ከ66 በፊ
ተም ሆነ በኋላ ከድርጅቱ በየጊዜው ከለቀቁትና ከተወገዱት አባሎች በስተቀር /የጓዶቹ
ፍፁም ለአብዮት መሰለፍና አብዮቱን ከራስ ጥቅም በማስቀደም ለመታገል ዝግጁ መሆን ነበር::
ወደፊትም ቢሆን፣ እያንዳንዱ ጓድ ለአብዮቱ እስከሞት ድረስና ህይወቱን ጭምር አሳልፎ ለመ
ስጠት ዝግጁ እስከሆነ ድረስ፣ ድርጅቱም ራሱን ከክለሳ እስከጠበቀ ድረስ፣ የመስመር ተገለ
ሄስና ገለሄስ ፈጽሞ የሚያስፈሩ ነገሮች አይሆኑም::ከድርጅታችን አጭር የህይወት ታሪክ በ
ገለጸ ለማየት እንደሚቻለው ሁሉ፣ እነዚህ አጠነከሩን፣ ወደፊት እንድንገሰግስ አደረጉን እንጂ፣
አላዳከሙንም፣ አልበታተኑንም::ስለሆነም፣ ድርጅታችን መጠናከሩንና የበለጠ አስተማጸስን ጫ
ድረጉን ይቀጥላል::

ከግንቦት 67 እስከህዳር 68 የነበረው ጊዜ በኢትዮጵያ አብዮት የሰስት አመታት
ታሪክ ውስጥ በጣም አስቸጋሪ ወቅት ነበር::ባንዱ በኩል፣ ደርጉ የመፀሰፀል ጠበቆን በማስ
የት፣ በሰራተኛው ማህበር ላይ፣ በዘማቾች፣ በተራማጅ የመሬት ይዞታ ሰራተኞችና አስተዳዳሪ
ዎች ላይ፣ በተማሪዎችም ላይ በርከት ያሉ የጭቆና እርምጃዎችን ወሰደአል::ዘማቾች ተጥቀ
ያስፈቶትን የመሬት ከበርቴ መልሶ በማስታጠቅ፣ የሸፈቱትን ምህረት ተደርጎልሃል እያለ በመ
መለስና እንደገና ፀረህዝብ ድርጊቶችን እንዲፈጽም እድል በመስጠት፣ በብዙ ቦታዎች ከአድሃ
ሪያዊ ጋር ተሰልፍአል::በመስከረም ወር 68 በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰራተኞች ላይ ደርጉ
ተደናብሮ የወሰደው እርምጃና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ፍፁም ፀረህዝብ ነበሩ::በመቀሰለው በ
ደርጉ ውስጥ የቀኝ አዝማሚያዎች ያበፈፈበት ወቅት ነበር::በሌላ በኩል ደግሞ የደገፊው ቡ
ድን የአንጃል ጀብደኝነት ድርጊቶች፣ በሰራተኛውና በወጣቱ ውስጥ የነዛው ወዥንብርና የድንፋታ
መንፈስ ለደርጉ የቀኝ ክንፍ አመቺ ሁኔታን ፈጥሮ ነበር::በዚሁ ሁሉ ላይ ደግሞ የተለመደው
የክረምት የእህል እጥረትና የዋጋ መናር ሲጨመር በመቀሰለው አብዮቱ እንዳይ ቀለበስ ከሚያሰ
ጋበት ሁኔታ ላይ ደርሶ ነበር::"የአብዮታዊ ሄስ" መመሪያችን ከፈተና ላይ የወደቀበት
ወቅት ነበር::ይሁንናም፣ የወቅት ለጊዜው አስቸጋሪ ቢሆንም ዘላቂነት ሊኖረው እንደማይችል
በመገንዘብ፣ ድርጅታችን በመስመሩ ፀንቶ ትግሉን ለማፋፋም ችሎአል::የደርጉን ወላዋይነትና
የደገፊውን ቡድን የአንጃል ጀብደኝነት ድርጊቶችን ማጋለጥና የአብዮቱን አቅጣጫ ለሰፊው ህዝብ
መጠቆም የወቅቱ ትክክለኛ ታክቲክ ነበር::

ይህ ታክቲክ ዛሬም ትክክል መሆኑን እናውቃለን::ዛሬም በደርጉ ውስጥ የቀኝ አ
ዝማሚያዎች አሉ::ዛሬም የደርጉ ቀኝ ክንፍና ደገፊው ቡድን እንዲሁም የመሳፍንት ተከፋ ለ
ዘውድ ቡድን በተግባር ሊተባበሩና ቀለበሳን ሊያመጡ እንደሚችሉ እናውቃለን:: ነገር ግን ዛ
ሬም እንደተናገርነው የሰፊው ህዝብ መንቀት መደራጀትና መታጠቅ እንገራጭ የሰው የአብዮቱ ጉዳና
ስለሆነ በ"አብዮታዊ ሄስ" መመሪያችን ለሰፊው ህዝብ ያለአንዳች አደርባይነት ትክክለኛ
ውን የአብዮቱን አቅጣጫ እንጠቁማለን::

የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ በታሪክ አይን ሲታይ በጣም አጭር በሆነ
ጊዜ ውስጥ ፈጽሞ ሊናቁ የማይችሉ ድሎችን አግኝቶአል::ከነዚሁ ውስጥ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ
የሀል፣ የዘውድ አገዛዝ መገርሰስ፣ የገጠር መሬት፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች፣ በርከት
ያሉ የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች የህዝብ ንብረት ተደርገዋል::በሃይለስላሴ ዘመን ስሙን
እንኳ ማንሳት እንደወንጀል ይቆጠር የነበረውና ፅሁፍቱ እየተሰበሰቡ ይቃጠሉ የነበረው ሶ
ሻሊዝም በሰፊው በመስፋፋት ላይ ይገኛል::ዛሬ ለኢትዮጵያ ግልጽ የሆነ የብሄራዊ ዲሞክራሲ
ያዊ አብዮት ፕሮግራም ወጥቶ በዚያ ውስጥ የብሄረሰቦች የራስን እድል የመወሰን መብት በይፋ
ታውቆአል::. . . እነዚህና ሌሎችም ትላልቅ ድሎች በዚሁ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊገኙ የቻሉበት
ምክንያት ምንድነው? የተገኙትስ ድሎች የቃል ብቻ ናቸው ወይንስ በገብርም ይታያሉ?

የኢትዮጵያ አብዮት እንቅስቃሴ ያስገኛቸውን ድሎች በማመለከተው በኩል፣ ኢምፔሪ
ያሊዝምና አድሃሪዎች ሁሉ፣ የኢህአፓንም ደገፊዎች ጨምሮ፣ ያላቸው አቋም አንድ ነው::በኢ
ትዮጵያ ምንም ያህል ለውጥ አልተደረገም የሚሉ አሉ::ወይንም ደግሞ የተደረጉት ለውጦች አ
ገሪቱን ከዉለማ የፋሺስታዊ አገዛዝ ስር አስገቡዋት፣ ስለዚህም የኢትዮጵያ ህዝቦች ከሁሉ
አስቀድሞ ይህንን "የደርግ ፋሺዝም" ተዋግተው ማስወገድ አለባቸው ይላሉ::ወይንም ደግሞ፣
የተደረጉት ለውጦች በቃሉ፣ በአዋጅ ደረጃ ብቻ እንደቀሩ፣ ግን ለጊዜው ሰፊውን ህዝብ ለመ
ደለል እንዲያገለግሉ የታቀዱ ናቸው ይላሉ::ይህ ሁሉ ወቸስ ኢምፔሪያሊዝምና የወደፊት መደ
ቦች የራሳቸውን የመለሻ መንገድ የሚያዘጋጁበት፣ የሌሎም ህዝቦችን አስተያየት የሚያወናበ
ዱበት ስልት እንጂ ከተጨባጩ የኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር በሩቅም እንኳን የማይመሳሰል ነገር ነው::

የኢትዮጵያ ህዝቦች በርግጥ የማይናቁ ድሎችን አግኝተዋል::የሰፊውን ህዝብ ተግ
ሎች አቀነባብሮ የሚመራ ጠንካራ አብዮታዊ ድርጅት ባለለበት ሁኔታ፣ የኢትዮጵያ አብዮት እ
ስካሁን እነዚህን ድሎች ማግኘቱና ሳይቀለበስም መቆየቱ ብዙውን የውጭ ተመልካቾች ሳያስደንቅ
አይቀርም::ድሎቹ የተገኙበትን ምክንያት እንደሚከተለው ለማቅረብ ይቻላል:-

.../10

አንደኛ፣ የኢትዮጵያ የውስጥና ውጭ ሁኔታዎች ለለውጥ አመቺ ነበሩ፡፡ ባንድ በኩል የቀደሞው ስርአት ፍፁም የበሰበሰ ከመሆኑ የተነሳ፣ የኢትዮጵያን ህዝቦች የተፋፋመ ትግል —የገበሬዎችን አመጾች፣ የዐዛደሩን እንቅስቃሴ፣ የተማሪዎችን አብዮታዊ ትግሎች፣ የብሄረሰቦችን የመብት ትግል— ከቁጥጥሩ ስር ለማድረግ አልቻለም፡፡ ከዚህም የተነሳ በገዥ መደቦች በራሳቸው ውስጥ፣ ማለትም በፊውዳሊዝም መደብና በቢሮ ከበርቴው መደብ መካከልና በያንዳንዱም መደብ ውስጥ በተለያዩ ቡድኖች መካከል፣ ሃይለኛ የስልጣን ሽሚያ ነበር፡፡ ገዥ መደቦች እንደቀደሞው በፀጥታ ለመግዛት አልቻሉም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የቀደሞውን ስርአት አጥብቆ ደግፎ ይዞት የነበረው ያሜሪካን እምፔሪያሊዝም እራሱ በኢንዶቻይና ህዝቦች ትግል ተሸንፎ ሃፍረትን ከተከናነበ በሗላ፣ በብዙ የውስጥና የውጭ ችግሮች ተወጥሮ ተይዞ ስለነበር፣ በኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ አተኩሮ የቀደሞዎቹን ገዥ መደቦች ከውድቀት ሊያድናቸው ከማይችልበት ሁኔታ ላይ ነበር፡፡ ስለዚህም፣ የየካቲት እንቅስቃሴ ፈንድቶ በጥቂት ዐራት ውስጥ ከሁለቱም ሃይሎች ቁጥጥር ውጭ ሊሆን ችሏል፡፡

ሁለተኛ፣ የንጉስነገስቱ የመጨረሻ መሳሪያዎች የነበሩት የጦር ሃይሎች በስርአቱ ላይ አፈሙዛቸውን ማዞራቸው ለለውጡ ወሳኝ ነገር ነበር፡፡ የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ እራሱ ጭቁን ሆኖ ሰፊውን ህዝብ የሚጨቁን ከመሆኑም በላይ፣ እርስ በርሱ የተከፋፈለና በተለይም ለንጉስነገስቱ "ፍፁም ታማኝ" የሆነ ሃይል ነበር፡፡ ንቅናቄው ከደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ አልፎ ወደፖለቲካ ጥያቄ ሊዛወር የቻለው በውስጡ የነቃ ወጣት መኮንኖችና ባለሌላ ማእረጎችም ስለነበሩና እነዚህም የስርአቱን መበስበስ በመገንዘብ፣ በቁራጥነት በመነሳሳት መላ ሰራዊቱን ለማስከተል በመቻላቸው ነው፡፡ ያለነዚህ ቁራጥ ታጋዮችና ያለመለዮ ለባሹ ምንም ያህል ለውጥ ሊመጣ ባልቻለ ነበር፡፡

ሶስተኛ፣ በሰኔ 66 የጦር ሃይሎች አስተባባሪ ደርግ በቆመበት ወቅት፣ ጥቂት ተራማጆችና አገርወዳድ ግለሰቦች ደርጉን በአሳብ ሲረዱት እንደቻሉ ይታወቃል፡፡ በተለይ ግን ከታህሳስ—ጥር 1967 ጀምሮ፣ በሃቀኛ የኢትዮጵያ ተራማጆችና በደርጉ የግራ ክንፍ መካከል የገቢር ህብረት ተፈጥሮ ነበር፡፡ ስለሆነም፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ የተባሉትን ድሎች እንዲያገኝ ካደረጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ የሃቀኛ ተራማጆች ከደርጉ ጋር መሰለፍ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ አብዮታውያን ይህንን ቁራጥ እርምጃ ባይወስዱና እንደኢህአፓ ጀብደኞች "በማያቋርጥ ተቃውሞ" ቢፀኑ ኖሮ፣ አብዮቱ በርግጥ ይቀለበስ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ አብዮት የማይናቁ ድሎችን ተቀዳጅቷል፣ ግን እነዚህ ድሎች በቀላሉ የተገኙ አልነበሩም፡፡ የመሬት ላራሹ አዋጅ በየቦታው ዐጊያዎችን በመፍጠሩ ብዙ ጭቁን መለዮ ለባሾች፣ አዝማቾች፣ ዘማቾች፣ የመሬት ይዞታ ሰራተኞችና አርሶአደሮች ህይወታቸውን መስዋእት አድርገዋል፡፡ ይህንን አዋጅና ሌሎቹንም በመቃወም የተነሳሱት አድሃሪያን በየቦታው በመጠኑም ቢሆን ተደምስሰዋል፡፡ ባንድ ጊዜና አገርአቀፍ የሆነ የርስበርስ ጦርነት አይሁን እንጂ በየቦታውና በየጊዜው በአብዮትና በፀረአብዮት ሃይሎች መካከል ትላልቅ ግጭቶች ተደርገው ሰፊው ህዝብ ብዙ መስዋእቶችን ተቀብሏል፡፡ መኢሶንም በትግሉ ሜዳ ካሰማራቸው ቁራጥ ታጋዮች ውስጥ በርከት ያሉ ጓዶችን አጥቷል፡፡ ይሁንናም፣ ለተገኙት ድሎች ሰፊው ህዝብ ብዙ መስዋእትን ያደረገ ቢሆንም፣ እነዚህ ድሎች አሁንም ገና ስር አልሰደዱም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ነቅተው፣ ተደራጅተውና ታጥቀው ያገኙዋቸውን ድሎች እስከመጨረሻው ለመጠበቅና አዳዲስ ድሎችንም ለመቀዳጀት ገና ብዙ መንገድ ይቀራቸዋል፡፡ የዐዛደሩን ፓርቲና በዚህም ፓርቲ የሚመራ አብዮታዊ ግንባርን ፈጥረው፣ ፊውዳሊዝምን፣ እምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ደምስሰው የመንግስትን ስልጣን በእጃቸው እስኪያስገቡ ድረስ፣ ያገኙዋቸው ድሎች ዘላቂ ሊሆኑ እንደማይችሉ ግልጽ ነው፡፡

ይህንን ስለሚያውቁ፣ የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች ባሁኑ ወቅት አብዮቱን ለመቀልበስ በመሯሯጥ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነ መንገሻ ስዩም — ነጋ ተገኝ — አሊ ሚራህ /የኢዲዩ መሪዎች/ በእምፔሪያሊዝምና በአንዳንድ አድሃሪ የአረብ መንግስታት ተገዝተው፣ ከኢ.ኤል.ኤፍ. ጋር ግንባር ፈጥረው፣ አብዮቱን በመክበብ ላይ ይገኛሉ፡፡ ኢህአፓም ከነርሱ ጋር ተሰልፏል፡፡ እነዚህ ሃይሎች የቢሮክራሲያዊ ከበርቴውንና የመሬት ከበርቴውን ፀረአብዮታዊ ስራዎችና ድርጊቶች ያቀነባብራሉ፡፡ በጎረቤት አገሮች ድጋፍን አግኝተዋል፡፡ የፀረአብዮቱ ዋና አላማ በኢትዮጵያ የተጀመረውን እውነተኛ የህዝቦች ነፃነት እንቅስቃሴ ርቆ ሳይሄድ ለመቀልበስና ኢትዮጵያ ተመልሳ በጨለማው ስርአት ስር ወድቃ፣ ደካማና ወደሗላ የቀረች አገር ሆና እንድትኖር ለማድረግ ነው፡፡

ይህንን የፀረአብዮት ሃይሎችን ሴራ ሊያከሽፍ የሚችለው፣ የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ የህዝብ ሃይል ብቻ ነው፡፡ መኢሶን ባሁኑ ሰአት የሚታገለው የዚህ አይነቱ ሃይል በተቻለ ፍጥነት እንዲፈጠርና እንዲጠናከር ሲሆን፣ የኢትዮጵያን አብዮት የአለም ፀረእምፔሪያሊስትና ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ሁሉ ከመደገፍ እንደማይቆጠቡ ያምናል፡፡

የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ የህዝብ ሃይል እንደሚያስፈልግ ለማሳወቅ ድርጅታችን በየእለቱ ሰፊ ቅስቀሳን እንደሚያደርግ በግልጽ እየታየ፣ አንዳንድ ሰዎችና ቡድኖች የመንግስትን ስልጣን እያያዙ በሚመለከተው በኩል መኢሶን ቁልጭ ያለ አቋም የለውም እስከማለት ይደርሳሉ! የኢትዮጵያ መለዮ ለባሹ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ለአብዮቱ እስካሁን ያደረጉት አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ መሆኑንና ወደፊትም ብዙ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ቢያምንም፣ እነዚህ ሃይሎች እንዳሉ እስከመጨረሻው ለአብዮቱ ይቆማሉ በሚለው የህልም እንጀራ ድርጅታችን ፈጽሞ አያምንበትም፡፡ በደርጉ ውስጥም ሆነ በመለዮ ለባሹ ውስጥ ያሉት አብዮታዊና ፀረአብዮታዊ ሃይሎች ሰልፋቸውን ለይተው የሚፋጠጡበት ወቅት በርግጥ ይመጣል፡፡ ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ በየእለቱ ይበልጥ መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ ያለበት፡፡

ባጭር ጊዜ ሲታይ፣ ድርጅታችን የሚታገለው ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መታወቅ፣ ለቢሮክራሲው መሻሻል፣ ለተራማጆች ህብረትና ለወዛደሩ ፓርቲ መፈጠር ነው፡፡ የድርጅታችን ባስተሳሰብም ሆነ በሰው ጉልበትና በድርጊት መጠናከር ለወዛደሩ ፓርቲ መፈጠር ዋስትና ነው፡፡ የተራማጆችን ህብረትና የወዛደሩን ፓርቲ እንፈጥራለን፡፡ ድርጅታችን በያዘው ትክክለኛ መስመር ቆርጦ ከገፋ፣ ግንኙነቱንም መስፋፋቱንም ሳይፈራ መሰናክሎችን ሁሉ ካሸነፈ፣ ከሰፊው ህዝብ ጋር በጥብቅ ከተሳሰረና ማርክሲዝም–ሌኒኒዝምን የድርጊቶቹ ሁሉ መመሪያ ካደረገ፣ ለኢትዮጵያ አብዮት የሚጠበቅበትን ድርሻ በርግጥ ያበረክታል፡፡

የተራማጅ ሃይሎች ህብረት ይመሰረታል!

ፀረአብዮታውያን ይደመሰሳሉ!

ሰፊው ህዝብ ያሸንፋል!